# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 204 ሚያዝያ 4 2004 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የወያኔ ልማት በድሆች ላይ ላይ የመጣ ጥፋት ሆኗል። በዘር ላይ በተመሠረተ አድልዎ የተፈጠረው የሃብት ልዩነት እጅግ ሰፍቷል። ይህ ራሱ ወደ ከፋ የእርስ በርስ ግጭት ሊወስደን ይችላል። የግጭት ምክንያቶች በዝተዋል። ስለዚህም ጊዜ የለንም።
በግንቦት 7 እምነት አገራችንን ለማዳን የቀረን ጊዜ ትንሽ፤ በጣም ትንሽ ነው። ስለዚህም በዚህ ወቅት ልቦቻችንና ክንዶቻችንን አስተባብረን በመለስ ዜናዊ ፋሽስታዊ አገዛዝ ላይ እናንሳ ይላል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዜጎችን በዘራቸው ምክንያት ከሚኖሩበት ማፈናቀል በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት በሰብአዊ ፍጡር ላይ በሚፈጸም ወንጀል የሚያስከስስ ጥፋት መሆኑ ተገለጸ

የተባበሩት መንግሥታት በሩዋንዳ የተካሄደውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ለማስቻል አቋቁሞ በነበረው አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ላይ በዋና አቃቤ ህግነት ያገለገሉት የአለም አቀፍ ህግ ምሁር ዶ/ር ያዕቀብ ሃይለማሪያም፤ በቤንች ማጂ ዞን ጉራ ፈርዳ ወረዳ በአማራነታቸው ምክንያት ብቻ እንዲባረሩ የተደረጉ ዜጎች ጉዳይ የሀገሪቱ ህገመንግሥት አንቀጽ 32 ድንጋጌዎችን ጨምሮ የተለያዩ አለም አቀፍ ህጎችን የሚጻረር በሰብአዊ ፍጡር ላይ በሚፈጸም ወንጀል ሊያስከሥስ የሚችል መሆኑን ከአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋር ባካሄዱት ቃለ መጠይቅ ገለጹ።

እርሳቸው በሩዋንዳ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት አቃቤ ህግ ሆነው በሰሩበት ወቅት የሁቱ ባለሥልጣኖች ቱትሲዎችን ያለውደታቸው ከቦታ ቦታ በማዘወራቸው ክስ ተመስርቶባቸው እስከ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንደተፈረደባቸው የገለጹት ዶ/ር ያዕቀብ፤ ወንጀሉ በሰብዕና ላይ ከሚፈጸም ወንጀል ከፍ ብሎ በዘር ማጥፋት እስከማስጠየቅ እንደሚደርስና የኢትዮጵያ ባለስልጣኖች በአጥፊዎች ላይ እርምጃ መውሰድ ከተሳናቸው በተባበሩት መንግሥታት በኩል ዘሄግ በሚገኘው አለም አቀፍ ፍርድቤት የክስ ፋይል ሊያስከፍት የሚችል ወንጀል መሆኑን አስታውቀዋል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ራሱ ጽፎ ባጸደቀው ህገመንግሥት አንቀጻ 32 የተረጋገጠውን የዜጎች በየትኛውም የአገሪቱ ክልል ተዘዋውሮ የመኖር መብታቸውን የገፈፈ ወንጀል የተፈጸመባቸው የአማራ ተወላጆች ጉዳይ ሁቱዎች በ1990ዎቹ በቱቲስ ተወላጆች ላይ ከፈጸሙት ወንጀል ጋር ያመሳሰሉት የአለም አቀፍ ህግ ምሁሩ ዶ/ር ያዕቀብ ዜጎችን በሃይል ከመኖሪያ ቦታቸው ማባረር “ዲፖርተሽን” በህግ ትርጉም ከዘር ማጥፋት እርምጃዎች አንዱ እንደሆነም አክለው አረጋግጠዋል።

በደቡብ ክልል በወያኔው ቅምጥ ፕሬዝዳንት በሽፈራው ሽጉጤ ፊርማ በግፍ የተባረሩ እነዚህን የአማራ ተወላጆች የአማራ ህዝብ ተወካይ ነኝ በማለት ክልሉን ለወያኔ ጥቅም እያስገዛ ያለው ብአዴን አስገድዶ ወደ የትውልድ ስፍራቸው እያጓጓዘ መሆኑን መዘገባችን ይታወሳል።

## ቢጋምቤላ የሰፈረው የወያኔ ጦር በክልሉ ተወላጆች ላይ የእስርና የግዲያ ወንጀል እየፈጸመ መሆኑን የአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ አጋለጠ

ለአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ "ጋምቤላ ተጨንቃለች፤ በሚል ርዕስ ባወጣው ዘገባ በክልሉ የተሰማራው የወያኔ ጦር ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 29 ቀን በጥይት ደብድቦ በገደለው የ18 አመት ወጣት መቃብር ላይ የተገኙ የአካባቢው ተወላጆች "በመሬታችሁ ላይ ሙቱ በመሬታችን ላይ እንሙት" የሚል መልዕክት ማስተላለፋቸውን ገልጾአል።

እንደ ጋራ ንቅናቄው መረጃ ቴዲ ኩል ኡማን የተባለ የ12ኛ ክፍል ተማሪ በአካባቢው ባህል መሠረት አዲስ ለተወለደ ህጻን ሥም ለመስጠት በተዘጋጀ ክብረ በአል ላይ እያለ 5 ነፍጥ ያነገቡ የመከላኪያ ሠራዊት አባላት ወደ ስፍራው በማምራት ወደ ውጪ ካስጠሩት በኋላ መታወቂያውን እንዲያሳይ በሃይል ይጠይቁታል። በጥያቄው የመገረም ስሜት የተሰማው ወጣት ቴዲም ምንም ወንጀል ያልፈጸመ የከተማው ሰላማዊ ነዋሪ መሆኑን ገልጾላቸው ወደ ነበረበት ዝግጅት ለመመለስ ሲራመድ ከበስተጀርባው ተኩሰው ገድለውታል ያለው የጋራ ንቅናቄው ዘገባ፤ ሰላማዊ ዜጋን ከአጠገባቸው ጠርቶ የገደለው የመከላኪያ ሰራዊት ለምን እንዲህ አይነት ጨካኝ እርምጃ እንደወሰደ በወቅቱ ያልገባው ህዝብ ተደናግጦ ጩኼቱን ሲያቀልጥ ገዳዮች አስከሬኑን ይዘው ለመሄድ ያደረጉትን ሙከራ የሟች አብሮ አደግ አስከሬኑን አቅፎ አልሰጥም በማለት እንዳስጣለና በዚህም ቁጭት ከግዲያው ወንጀል ጋር ይያያዛል ተብሎ በተጠረጠረ ሰው ንብረት ላይ የአካባቢው ህዝብ እርምጃ መውሰዱን ገልጾአል።

የጋምቤላ ህዝብ ከመሬቱ ላይ በሃይል መፈናቀሉን መቃወም ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በክልሉ የተሰማራው የወያኔ ጦር በህዝቡ ላይ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግዜ

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ስኖዶስ በገዳማትና አድባራት ላይ እየተፈጸመ ያለውን ጥፋት በመኮነን መግለጫ አወጣ። ገዳማት እየወደሙና የአባቶች አጽም ካረፈበት እየተፈናቀለ የዘንድሮውን ትንሳኤ በአል በደስታ ማክበርስ እንዴት ይቻለናል? ሲል ጠየቀ

ህጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በዋልድባ ገዳም ላይ እየተፈጸመ ያለውን ጥፋት በመቃወም ባወጣው መግለጫ ገዳሙን ከወያኔ ጥፋት ለመከላከል ሁሉም ወገኖች እንዲነሱ አሳስቦ መከፋፈላችን የሚጠቅመው ዘረኛውንና ከፋፋዩን የወያኔ ቡድን መሆኑን በመገንዘብ የህዝብና የሃይማኖት ጠላት በሆነው ጠባብ የገዢ ቡድን ላይ በህብረት እንነሳ ብሏል።

ዋልድባ ከአስራ ሶስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የታወቀ ገዳም መሆኑን በመጥቀስ እስከ አሁን በዘረኛው የወያኔ ቡድን ከመደፈሩ በስተቀር በኢትዮጵያ ጠላቶች እንኳን ያለመደፈሩን ያስታወሰው መግለጫው ይህ ድርጊት የወያኔን የጥፋት ደረጃ ጣሪያ መንካት የሚያመላክት ነው ብሏል።

ወያኔ እስካለ ድረስ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በሰምም በመልክዓ ምድርም አትኖርም፤በመሆኑም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል የሚፈልግ ወገን ሁሉ ይህንን ዘረኛ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ መረባረብ ያለበት ጊዜ አሁን ነው_ እንደ መግለጫው።

በፖለቲካና በሀይማኖት ልዩነት ምክንያት በጠላትነት የሚተያዩ ወገኖች ሁሉ ህዝብ ከማለቁና ሀገር ጨርሶ ከመጥፋቱ በፊት ልዩነቶቻቸውን በማቻቻል በጋራ ጠላታቸው ወያኔ ላይ እንዲነሱ ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው ተማጽኗል።

በተለይም በአንድ እምነት ውስጥ ሆነው የዘረኛውን የወያኔ ድጋፍ በመተማመን ከወገኖቻቸው ጋር የተለያዩ ወገኖች በሙሉ ተቃውሞአቸውን የችግራቸው ምንጭ በሆነው ከፋፋይና ጠባብ ቡድን ላይ በማጠናከር ችግሮቻቸውን በውይይት ለመፍታት እንዲተጉ በመጠየቅ ለዚህ ዓይነቱ ዓላማም ደጋፊያቸው መሆኑን አስታውቋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በዘረኛው መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በሽብረተኝነት ተወንጅለው ከወያኔ ችሎት እየተመላለሱ ያሉት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና አንዱ አለም አራጌ የፈጠራ ክሱን የሚያጋልጥ የቪዲዮ ማስረጃቸውን አቀረቡ

በፈጠራ ክስ በተወነጀሉ ለውጥ ፈላጊ ዜጎች ላይ ፍርድ ለማሰጠት የወያኔ አቃቢ ህግ ቆራርጦ ያቀረባቸውን የቪዲዮ ማስረጃዎች ምንነት እንዲታይላቸው አጥብቀው ሲሟገቱ የሰነበቱት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ እና አንዱአለም አራጌ በተናናናው ዕለት ተፈቅዶላቸው የተከሰሱበትንና በህገወጥነት የተፈረጀውን ንግግራቸውን ሙሉ ቃል የሚያሳይ ቪዲዮ ማሳየት መቻላቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከስፍራው በላከልን ዘገባ ገለጸ።

የወያኔ አቃቤ ህግ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ የሆነው አንዱአለም አራጌ እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የመለስ አገዛዝ እንዲወገድ የአመጽ ጥሪ መቀስቀሳቸውን ያሳይልኛል በማለት የተቆራረጡና ለመስማት የሚያስቸግሩ የቪዲዮ ማስረጃዎችን በማቅረቡ ምክንያት ትክክለኛውና ሙሉው የንግግሮቹ ክፍል እንዲቀርብና እንዲታይላቸው አጥብቀው ሲከራከሩ የቆዩት ተከሳሾች አቃቢ ህግ ተብዬው ሙሉው ቪዲዮ እንዳይቀርብ ያደርግ የነበረውን ተጽዕኖ ተቋቁመው እንዲታይላቸው ማድረግ መቻላቸው በራሱ ትልቅ ድል እንደሆነ የፍርድ ቤቱን ውሎ የተከታተሉ ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።

እንደዘጋቢያችን መረጃ ቪዲዮው ሊቀርብ የቻለው ጉዳዩን እንዲያስችሉ በወያኔ ከተመደቡ ዳኞች ውስጥ የማህል ዳኛው አቃቢ ህግ የራሱን ማስረጃዎች ያቀረበ በመሆኑና ተከሳሾችም የራሳቸውን ማስረጃ የማቅረብ መብት ያላቸው ስለሆነ ሊከለከሉ አይገባም በማለት ትእዛዝ በመስጠቱ እንደሆነ ታውቋአል።

ትናንት ሚያዚያ 3/2004 ዓ/ም በመከላከያ ማስረጃነት በቀረቡት ቪዲዮዎች እንደተመለከተው አንዱአለም አራጌ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የአፈና ስርአት በአረቡ አለም ከታየው ህዝባዊ አመጽ ጋር በማነጻጸር በኢትዮጵያ ውስጥም በሰላማዊ ትግል ለውጥ ማምጣት አስፈላጊ መሆኑን፣ ከሰላማዊ ትግል ውጭ ግን ሌሎች አማራጮች የማይሰሩ መሆናቸውን መናገሩን አረጋግጦአል። በጋዜጠኛ እስክንድር ነጋም በኩል የቀረበው የቪዲዮ ማስረጃ በተመሳሳይ ሁኔታ ወያኔ የፈበረከውን የውሸት ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ የሚያደርግ በመሆኑ በነጻ ሊፈቱና የሚፈረድ ዳኛ በአገሪቱ ቢኖር ኖሮ ሁሉም ያለ አግባብ እስከዛሬ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አገራችንን ለማዳን እንፍጠን፤ ጊዜ የለንም!!!

በደቡብ ኢትዮጵያ በቤንች ማጂ ዞን በጉራ ፋርዳ እና ሌሎች የዞኑ ወረዳዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የአማራ ክልል ተወላጆች በዓመታት ድካም ያፈሩትን ንብረት ተነጥቀው፤ ተደብደበውና ሰብዓዊ ክብራቸው ተደፍሮ በግፍ መባረራቸው ኢትዮጵያዊያንን ያስቆጣ ጉዳይ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ይህ ዓለም ዓቀፍ ትኩረት የሚሻ ወንጀል ነው ብሎ ያምናል። ይህ የዘር ማጥፋት ወንጀል ነው። ይህ ወንጀል የተፈፀመው የመንግሥትን መዋቅር በተቆጣጠረ ወንበዴ መሆኑ አደጋው ጥልቅና ሰፊ እንዲሆን አድርጎታል።

የሰሞኑ ክስተት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘረኝነት እንደምን ያለ ከፍተኛና አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሱን አመላካች ነው። ከዚህ በላይ ምን እስክንሆን ወይም ምን እስከምንደረግ እንደምንጠብቅ መጠየቅ ያለብን ራሳችንን ነው።

ለመሆኑ

- ዛሬም እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ ተጫጩኸን ዝም ነው የምንለው?
- ዛሬም በየራሳችን ጎራ ላይ ቆመን አቅራርተን ነው የምንመለሰው?
- ዛሬም ራሳችንን እንደቁማር መጫወቻ ካርታ በመጥወዝ ጊዜና ጉልበት እናጠፋለን?

ወይስ

- ይህን ግፍ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲያበቃ ተጨባጭ የሆነ የተግባር ሥራ ውስጥ በመሳተፍ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ላይ ክንዶቻችንን እናነሳለን?

ምርጫው የእያንዳንዳችን ነው።

በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለው በደል ዘልቆ የተሰማን መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም ግን ስሜት ብቻውን በቂ አይደለም። ቁጭት ብቻውን በቂ አይደለም። ድርጊት ነው የሚያስፈልገው። ተግባር ነው የምንፈልገው። ወያኔን ድርጊት እንጂ ቁጭት አያስቆመውም።

ሌላም አሳሳቢ ጉዳይ አለ።

ወያኔን ዛሬ በዚህ ካላስቆምነው ነገ ከዚህም የባሰ ነገር ውርደት ሊመጣ ይችላል። ወያኔ ከዚህ በፊት በደሴ አርሴማ ማርያም ቤተክርስቲያን ግንባታ ሰበብ ክርስቲያንና ሙስሊምን ለማጣላት ሞክሮ ምዕመናኑ ባሳዩት መቻቻል ምክንያት እንደከሸፈበት የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ወያኔ ሕዝብን በሕዝብ ላይ ለማነሳሳት ብዙ ጊዜ ጥሯል። እስካሁን አልተሳካለትም።

አሁንም የደቡብ ኢትዮጵያን ገበሬ በሰሜን ኢትዮጵያ ገበሬ ላይ ለማነሳሳት ወያኔ ግልጽ ቅስቀሳ እያደረገ ነው። በቤንች ማጂ የወያኔ ካድሬዎች አማርኛ ተናጋሪ አርሶ አደሮችን "ወራሪዎች፣ ነፍጠኞች፣ ዘራፊዎች" እንደሆኑ አድርገው የአካባቢውን ነዋሪዎች ሲቀሰቅሱ ቆይተዋል፤ አሁንም እየቀሰቀሱ ነው።

"ሊዘርፍህ፤ መሬትህን ሊቀማህ የመጣ ነው፤ በለው፤ አሳደው …" እያለ በግልጽ የሚቀሰቅሱ ካድሬዎች እያሉ የቤንች ማጂ አርሶ አደሮች በአማርኛ ተናጋሪ አርሶ አደሮች ላይ ክንዳቸውን አለማንሳታቸው እጅግ የሚያስመሰግን ነው። ከዚያም አልፎ የአካባቢው አርሶ አደሮች በአማርኛ ተናጋሪ አርሶ አደሮች ላይ እየተደረገ ያለውን ግፍ ተቃውመዋል። አንዳንዶች የተቃውሞ ድምፃቸውን በግልጽ በአደባባይ በማሰማታቸው በወያኔ ታጣቂዎች ተደብድበዋል፤ እስካሁንም የታሰሩ አሉባቸው። ይህ ልናበረታታው የሚገባ ተስፋ ሰጪ ነገር ነው።

ይህ የሕዝብ ለሕዝብ መከባበር ምን ያህል ይቆያል? በዘርና በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ጠብን ሆን ብሎ የሚቆሰቁስ እኩይ ኃይል የመንግሥት ሥልጣን በተቆጣጠረበት አገር ውስጥ የእርስ በእርስ መተላለቅ እንደማይመጣ ምን ማስተማመኛ አለን?

በግንቦት 7፣ የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የሁኔታዎች ትንተና መሠረት አገራችን በቋፍ ላይ ነች። እስካሁንም ያቆያት የሕዝቧ ቻይነትና አርቆ አስተዋይነት ነው። በጥባጭ የመንግሥትን ሥልጣን በያዘበት መቻቻል ሁሌም ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ግንቦት 7: "አገራችንን ለማዳን እንፍጠን፤ ጊዜ የለንም" የሚለው ይህ ተጨባጭ አደጋ የሚታየው በመሆኑ ነው። አደጋው ለሁላችንም በግልጽ ይታየን። አገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ የእርስበርስ ፍጅት አደጋ ውስጥ ነች።

አማርኛ ተናጋሪው ከደቡብ ኢትዮጵያ ሲባረር አማራ ክልል ውስጥ የሚጠብቀው የእርሻ ቦታ የለም። አማርኛ ተናጋሪው አገር የለውም፤ አማራ ውስጥም መንደር የለውም። እዚያም ደኑ ጋይቷል፤ የተቀደሱ ቦታዎች ተደፍረዋል፤ የቅዱሳን መካነ መቃብር ለሸንኮራ አገዳ ተብሎ ታርሷል። ከአንድ የአገሪቱ ጫፍ ተሰዶ እቀድሞው መንደሩ ሲደርስ የድሮ መንደሩ የለችም። ይህ ሕዝብ የት ይገባል? ምን ይሆናል?

አፋር ውስጥ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ለሸንኮራ አገዳ ምርት ሲባል ልቀቁ ተብለው መድረሻ አጥተዋል። አሁን የአፋር ሕዝብ አገር የለውም፤ መንደር የለውም። የአፋር ሕዝብ የት ይሄዳል? የሶማሊና የጋምቤላ ተወላጆችም አገርም መንደርም የላቸውም። የት ይገባሉ? ምን ይሆናሉ?

ኢትዮጵያዊያን ሁላችን አገርም መንደርም የለንም። የት ነው የምንገባው? ምንድነው የምንሆነው?

የወያኔ ልማት በድሆች ላይ ላይ የመጣ ጥፋት ሆኗል። በዘር ላይ በተመሠረተ አድልዎ የተፈጠረው የሃብት ልዩነት እጅግ ሰፍቷል። ይህ ራሱ ወደ ከፋ የእርስ በርስ ግጭት ሊወስደን ይችላል። የግጭት ምክንያቶች በዝተዋል። ስለዚህም ጊዜ የለንም።

በግንቦት 7 እምነት አገራችንን ለማዳን የቀረን ጊዜ ትንሽ፤ በጣም ትንሽ ነው። ስለዚህም በዚህ ወቅት ልቦቻችንና ክንዶቻችንን አስተባብረን በመለስ ዜናዊ ፋሽስታዊ አገዛዝ ላይ እናንሳ ይላል።

የግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዓላማ የመለስን አገዛዝ አስገድዶ ማስወገድ እና በምትኩ ፍትህ የሰፈነባት አገራችን ኢትዮጵያን መገንባት በመሆኑ ዛሬውኑ ይቀላቀሉት፤ አሊያም በተቻልዎት ሁሉ ትግሉን ይርዱ። አገራችንን ለማዳን እንፍጠን፤ ጊዜ የለንም!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ፋራህ ማሊም የተባሉት የኬንያ ፓርላማ ምክትል አፈጉባኤ በአገራቸው የተመደበው የወያኔ አምባሳደር ስለዲሞክሪሲ ባይገባው አይገርምም ምክንያት አምባገነንነት ከተንሰራፋበት ምድር በመምጣቱ ሲሉ ተሳለቁበት

በኬንያ የወያኔ አምባሳደር ሆኖ የተመደበው ሽምሰዲን ሮቤሌ አፈጉባኤው የሰጡትን አስተይየት በሚገባ ሳይረዳ ለትችት በመነሳቱ ስታንዳርድ በተባለው የኬንያ ጋዜጣ ላይ ሲሳለቁበት አምባገነንነት ከነገሰበት ጎሬቤት ኢትዮጵያ የመጣ በመሆኑ ዲሞክራሲያዊ አሰራር ባይገባው አይገርምም ማለታቸው ተዘግቦአል።

ሃሳብን በነጻነት መግለጽ ኬንያ ውስጥ ማንም ሊገፈው የማይችል በህግ የተረጋገጠ መብት ነው ያሉት አፈጉባኤው ፋራህ ማሊም ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው አፈና ምክንያት ዛሬ ከትግራይ፣ ከአማራና ከደቡብ አንዳንድ አካባቢዎች ውጪ ባሉ ሁሉም ክልሎች በጠመንጃ ወደ ስልጣን የመጣውን የህወሀትን ስርዓት ለመጣል የትጥቅ ትግል እየተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል።

አፈ ጉባኤው እንደሚሉት ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው፤ ማንኛውም የወያኔን ስርዓት የሚቃወም ሰው ማረፊያው ወህኒ፣ ስደት ወይም መቃብር መሆኑ ነው። ለዚህ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር፣ የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር፣ የቤኒሻንጉልና የጋምቤላ ህዝቦች ንቅናቄዎችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል ብለዋል።

ማሊሞ ይህን ያሉት ሽምሰዲን ሮቤል የተባለው የወያኔ አምባሳደር ስታንዳርድ በተባለው የኬንያ ጋዜጣ ላይ ባወጣው መጣጥፍ k24 ከተባለው ጣቢያ ጋር ያደረጉትን ቃለምልልስ አዛብቶ በመጠቀሙ በሰጡት ምላሽ ነው።

እንደ አፈ ጉባኤው አሁን አሁን በኢትዮጵያ ያለውን ጨካኝና አምባገነን ስርዓት በመሸሽ ወደ ኬንያ የሚጎርፉ ህገ ወጥ ስደተኞችን መመልከት የሚደንቅ አይደለም።አለመታደል ሆኖ ለምዕተ ዓመታት በሀገሪቱ የስልጣን መንበሩን የተቆናጠጡ ገዢዎች በሙሉ ወያኔን ጨምሮ እድሜያቸውን ለማራዘም የሚጠቀሙት ስልት አንድና አንድ ብቻ ነው - የጠመንጃ አፈ ሙዝ።

ስለ ዴሞክራሲ ሲነሳ ኢትዮጵያ ከኬንያ ፍጹም ተቃራኒ ጠርዝ ላይ ያለች ሀገር ናት፤ ኬንያ ውስጥ ዛሬ ማንኛውም የህዝብ አገልግሎት መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰራ ሰው ፕሬዘደንቱን ጨምሮ ለሚያከናውነው ተግባር ሀላፊነትና ተጠያቂነት አለበት። እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊተገበር ቀርቶ የሚታሰብ እንኳን አይደለም ብለዋል።

ኬንያ በአካባቢው ምርጥ የዴሞክራሲ ስርዓት የሰፈነባት ሀገር ናት ያሉት ፋራህ ማሊሞ በአምባገነን ስርዓት ከተቀየደችው ኢትዮጵያ የመጣው አምባሳደር በኬንያ ያለው ዓያነት ሊበራል ዴሞክራሲ በቀላሉ ይገባዋል የሚል እምነት የለኝም ነው ያሉት።

የኬንያ ህገ መንግስት አፍሪካ ውስጥ እጅግ የተሻለው የህግ ሰነድ ነው።የአፍሪካን ቀንድ ፖለቲካዊ ኤኮኖሚና ማህበራዊ ታሪክ እንደሚያውቅ ኬንያዊ ስገልጸው የእኛ ህገ መንግስት ቢያንስ ሃሳብን ለመግለጽ ነጻነት ዋስትና ይሰጣል ብለዋል።

አፈ ጉባኤው በዚሁ ምላሻቸው የኬንያ ጦር ሶማሊያ ውስጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አስመልክተውም ማብራሪያ ሰጥተዋል።

## ጠላቶቻችንን ለይተን እንወቅ !!!

መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊያንን ጠላት አድርጎ እንደተነሳ እስከዛሬ ድረስ የፈጸመው ተግባራቱ ቋሚ ምስክሮች ናቸው።እርሱ ጠላቶች አድርጎ የቆጠራቸውን የአገሪቷን ዜጎች ከሊቅ እስከ ደቂቅ "አሸባሪ" ብሎ የመከራ እንጀራን እንዲበሉ፤ የመከራ ጽዋንም እንዲጎነጩ እያደረገ ነው። ዛሬ እንደሰው ላስብበት የሚል አንድ ሰው በኢትዮጵያ ከተገኘ በመለስ ዜናዊ ህግ አሸባሪ ይባላል። እንዲህ የህዝቡን አሳር የሚያበዙት በአንድም በሌላ መንገድ በኢሕአዴግ ውስጥ የተሰባሰቡት ተራ አባላቱ ሳይሆኑ መለስ ዜናዊና በቅጥረኝነት የተሰማሩ ጥቂት ዘረኞች ናቸው።

መለስ ዜናዊ የፈጸመው ወንጀል የፈጠረበትን ቅዠት በኢሕአዴግ ዙሪያ በተሰባሰቡ ኢትዮጵያዊያን ውስጥ ሊያስተላልፈው የቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው። "በዚህች አገር ውስጥ ኢሕአዴግን የሚቃወሙ በመሉ ጠላቶቻችን ናቸው። ቢያሸንፉን በጠላት ላይ የሚደርሰው ሁሉ ይደርስብናል" እያለ የእርሱን ቅዠት የኢሕአዴግ አባላት በሙሉ እንዲጋሩት እየጣረ ነው። ይሄ የመለስ ዜናዊ ተንኮልና የብልግናው መገለጫ እንጂ ሂሊና ያለው ማንኛውም ተቃዋሚ በስመ ኢሕአዴግ የተሰበሰበውን ሁሉ በጠላትነት የሚፈርጅ ሆኖ አይደለም። ለተለያየ ዓላማና የግል ጥቅም የኢህአደግ መሪዎች በቃል የሚስብኩትን በጎ ነግሮች አምኖ አገሩንና ወገኑን እያገለገለ ያለ መስሎት ፓርቲውን የተቀላቀለ፤ አብሮትም ያለ እንዳለ ለማንም አልተሰወረምና። እነዚህ አይነቶቹ የህዝብ ወገኖች እዚያው ፓርቲው ውስጥም ሆነው መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ የተቃወማቸውን ሁሉ በሽብርተኝነት እየወነጀሉ ሲያፈናቅሉ፤ ሲያስሩና ሲያንገላቱ ልባቸው ከኛው ጋር እንደሚደማ፤ በሙስና የተጨማለቁ አለቆቹ ህዝቡን ቁም ሲቃይ ሲያበሉት እንደሚያዝን፤ በኑሮ ውድነቱ ምክንያት ከሚሰቃዩት ሚሊዮኖች እኩል ተጠቂ እንደሆነ ግልጽ ነውና በጠላትነት ሊፈረጅ ከቶውንም አይችልም።

ይልቁንስ ጠላቶቻችን አገሪቷን እየዘረፉ ህዝቧን በርሃብ አለጋ እንዲረግፍ የሚያደርጉት መለስና ጀሌዎቹ ናቸው። መለስና ቡድኑ ከአገሪቷ ሰርቀው ወደ ውጭ አገር ያሸሹት የገንዘብ መጠን 11.7 ቢሊዮን ዶላር መድረሱን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ነግሮናል። በዚህ ዝሪፊያ ውስጥ የተሳተፉት ደቂቃን የኢህአዴግ አባላት ሳይሆኑ የአገሪቷን የንግድና የሥልጣን ተቋማትን የተቆጣጠሩት መለስና በዙሪያው የተሰባሰቡ ዘረኞች ናቸው። ከዚህ ገንዘብ ውስጥም አዜብ መስፍን በአንዲት ጀንበር ብቻ ከሚሊዮን ዶላር በላይ አውጥታ እንዴት አድርጋ እንኳ መልበስ እንዳለባት የማታውቀውን ልብሶች መሸመቷን ከውጭ አገር ሚዲያዎች መስማታችንን እናስታውሳለን። በዚህም ምግባሯ በዓለማችን አሉ ከሚባሉ አባካኝ ሴቶች መካከል መፈረጇንም ሰምተናል። የአገሪቷ ጠላቶች እንዲህ ከድሆች ጉሮሮ እየነጠቁ ዜጎችን የሚያስርቡት ናቸው እንጂ በስመ ኢህአደግ ተገደውና አማራጭ አጥተው በገፍ የተቀላቀሉት የዋሃን አባላቱ አይደሉም።

ጠላቶቻችን ዛሬ አርሶ አደሮችን ከመኖሪያቸው እያፈናቀሉ መሬቶቻቸውን ለባእዳን አሳልፎ በመስጠት ሂደት ውስጥ ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ያሉ ኃይሎች ናቸው እንጂ በተፈናቃይ ወገኖቹ ላይ እየደረሰ ባለው ሰቆቃ እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ አንጀታቸው  እያረረ ቀን እየተጠባበቁ ያሉ የኢሕአዴግ አባላት አይደሉም። ገበሬውን እትብቱ ከተቀበረበት ቀዩ እየነቀሉ ሜዳ ላይ እንዲጣል ለማድረግ ጭካኔው ያላቸው መለስ ዜናዊና ጥቂት ቅጥረኛ ጀሌዎቹ ናቸው እንጂ ከገበሬው አብራክ ወጥተው በኢሕአዴግ ዙሪያ የተሰባሰቡ ብዙሃን እንዳልሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም።

"አማራ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው" የሚለውን መሪ ሃሳብ ስንቅና ትጥቃቸው አድርገው የሚሰሩት እነመለስ ዜናዊ ናቸው እንጂ የህዝብ ጠላቶች ደቂቃን የኢሕአዴግ አባላት አይደሉም።ኢሕአዴግ ውስጥ ያሉ ወገኖች በአማራና በትግራይ ህዝብ መካከል ጠላትነት እንደሌለ ያውቃሉ። እኛም እናውቃለን። የሁላችንም ጠላቶች በህዝቦች መካከል ጠላትነት ለመትከል የሚተጉት መለስና ዘራፊ ቡድኖች ናቸው እንጂ ሌሎች አይደሉም። መለስ ዜናዊ ዝሪፊያውንና በልዩ ልዩ መንገድ የሚፈጽማቸውን ወንጀሎችን የሚቃወሙትን ሁሉ ጠላቶች ናቸው ዓላማቸውም የኢሕአዴግ አባላትን ማጥፋት ነው እያለ የሚሰብከው ውሸቱን ነው።ማሰብ የሚችሉና የወገኖቻቸው በደል የሚያማቸው በኢሕአዴግ ዙሪያ የተሰባሰቡ ሰዎች የመለስን ቅዠት አይጋሩትም።ከወንጀል ነጻ እስከሆኑ ድረስ ከመለስ በኋላ የነጻነት ጎህ ሲቀድ በገዛ አገራቸው በነጻነትና በሠላም የመኖር መብታቸው ሙሉ በሙሉ የተከበረ ነው።

ደግመን ለማስታወቅ የምንወደው መለስ ዜናዊ ከዘረኛ ቡድኑ ጋር ሁኖ በዜጎች ላይ የሚፈጽመውን በደል የሚቃወሙት ኃይሎች ለኢሕአዴግ አባላት ጠላቶች አለመሆናቸውን ነው። ይልቁንም ተቃዋሚ ኃይሎች የሚታገሉት የኢህአዴግ አባላት በሙሉ እንደ ሰው ልጅ በነጻነት አስበው፤ሰብዓዊ መብታቸው ተከብሮ ከፍርሃት ነጻ ሆነው የሚኖሩባት አገር እንድትኖራቸው ለማድረግ ነው። ይህንን ሃቅ ጆሮ ያለው እንዲሰማው፤ የማስተዋል ችሎታ ያለውም እንዲያስተውል እንፍፈልጋለን።

የሁላችንም ጠላቶች ነጻነታችንን ገፈው፤ሰብዓዊ ክብራችንን አዋርደው፤ እንደሰው ማሰብ እንዳንችል አድርገው በዘርና በኃይማኖት ከፋፍለው፤ ረግጠውና አዋርደው ሊገዙን ሙሉ ኃይላቸውን በመጠቀም ላይ ያሉት መለስ ዜናዊና ዘራፊ ቡድኑ ብቻ ናቸው። በርሃባችን የሚጠግቡት፤በስደታችን የሚደሰቱት፤ በውርደታችን የሚኮሩት መለስ ዜናዊና ጀሌዎቹ ናቸው እንጂ ደቂቃን የኢሕአዴግ አባላት አይደሉም።

በአገራችን ላይ ጠላትነትን ያወጀው መለስ ዜናዊ ነው። ይህም አዋጅ ከሚቋቋመው በላይ ፍርሃትን ፈጥሮበታል። ይህ ግለሰብ አምነውት የተከተሉትን፤ እርሱ ግን ለከዳቸው ወገኖች የፍርሃቱን ቅዥት እንዲቃዥለት እየጣረ ነው። የመለስ ዜናዊንና የጥቂት ዘረኞችን *"ተቃዋሚዎች ሁሉ ጠላቶቻችን ናቸው"* የሚለውን ቅዥት መቃዥት ጅልነት ነው። ከዚህ ዓይነቱ ቅዥት ወጥቶ እነዚህን ዘረኛና ዘራፊ ቡድን ከተቆናጠጡበት ዙፋን ማውረድ እና መለስ ዜናዊን በቃህ ማለት ሰው የመሆን ግዴታ ነው። በአሁን ሰዓት የመለስን ዘረኛ ዲሪጊት አለመቃወም በታሪክ ፊት የሚያስጠይቅ ድርጊት ነው። ሁላችንም አንድ ሆነን ዘረኝነትንና ዝሪፊያን በቃ ለማለት አሁን ግዜው ደርሷል። ዛሬ መለስ ዜናዊ የሚፈጥረው የፍርሃት ቀንበር መሰበር አለበት። ለአገራችን ዜጎች ከራሱ ከመለስ በቀር ሌላ ጠላት የላቸውም። ሠላምም ያጣነው፤ርሃብም የተንሰራፋው፤ ነጻነታችንም የተገደበው በራሱ በመለስ ዜናዊ እንጂ በሌላ በማንም አይደለም።

የግንቦት ሰባት ንቅንናቄ ዋነኛው ጠላቱ ከሃዲውና ዘረኛው መለስ ዜናዊ የዘረጋው የዘረኝነትና፤ የዝሪፊያ መረብ እንጂ ነጻነት እኩልነት እና ለአገራቸው ክብር ዘብ ለመቆም የሚችሉ ዜጎች አይደሉም ብሎ ያምናል። ይህ የመለስ ዜናዊ የዘረኝነትና የዝሪፊያ መረብ እስከሚበጣጠስና ነጻነት፤ ፍትህ እና እኩልነት እስከሚሰፍን ድረስ ትግላችንን አጠናክረን እንቀጥላለን።ዓላማችን ነጻነት፤ ፍትህ፤ እኩልነት እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተገንብቶ ማየት ነው።ይህንንም ከግብ ለማድረስ ሰማይና ምድርን የሰራ አምላክ ከእኛ ጋር ነውና ዓላማችንን ከፍጻሜ ሳናደርስ አናፈገፍግም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን !!!**

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ስኖዶስ በገዳማትና አድባራት ላይ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በማያያዝም በሀገር ውስጥ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ድረስ በወያኔ ካድሬ አለቆቻቸውና በሙስና በተበላሸ አስተዳደር የሚሰቃዩና ነፍሳቸው የተጨነቀች ኦርቶዶክሳዊያን ወገኖች የዚህን ስርዓት ሁለ ገብ ጥፋት ለማቆም በያሉበት እንዲቃወሙ ጠይቋል።

እርዳታ ማድረግ ለሚችሉ እንደ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ ለዩኔስኮ፣የአፍሪካ ህብረት፣አፍሪካን ሄሪቴጅ ሶሳይቲ፣የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማህበርና ለመሳሰሉት ጩኸታችንን እያሰማን ነው ያለው የቅዱስ ሲኖዶሱ መግለጫ በሀገር ውስጥም በዓለም ዙሪያም ያሉ ወገኖች በሙሉ ልዩነቶቻቸውን በማቻቻል ይህን የህዝብና የሃይማኖት ጠላት የሆነ ዘረኛና ከፋፋይ የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በህብረት እንዲታገሉ ጥሪውን አስተላልፏል።

በመጨረሻም ቤተክርስቲያናችን በጨቋኞች እጅ ወድቃ፤ መብቷና ክብሯ ተገፎ፤ መናኝ ልጆቿ ለነፍስ አድን ጥሪ እየጮሁ በጨለማ አገዛዝ ሥር ወድቀው እንዴትስ የዘንድሮውን ትንሳዔ በአል በደስታ ልናከብር እንችላለን በማለት? የዘንድሮው ትንሳዔ በአል በገዳማቱ ላይ እየደረሰ ላለው ስቃይ መታሰቢያ ሆኖ እንዲከበርና ሁሉም የቻለውን አለማዊ እርዳታ እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፎአል።

## በጋምቤላ የሰፈረው የወያኔ ጦር በክልሉ ተወላጆች ላይ የእስርና የግዲያ ወንጀል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ተዘርዝሮ የማያልቅ ሰቆቃ እየፈጸመ ነው ያለው የጋራ ንቅናቄው መረጃ፤ በክልሉ የሚንቀሳቀሱትን አማጽያን ይዛችሁ አስረክቡ በሚል በሰላማዊ ነዋሪ ላይ እየደረሰ ያለው ግፍና መከራ ከእስርና እንግልት አልፎ እስከ ግድያ መድረሱን ዘርዝሮአል።

ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 29/2004 ዓ/ም የተገደለው የ18 አመት ወጣት የቴዲ አባት የዲማ ወረዳ ፖሊስ አዛዥ እንደሆነና አባትዬው የልጁ መገደል የተነገረው ትጥቁን እንዲፈታ ተደርጎ እስር ቤት ከተወረወረ ቦኋላ መሆኑን ዘገባው አክሎ አጋልጦአል።

## ዘረኛው የወያኔ ስርዓት ሆን ብሎና አቅዶ ከደቡብ ክልል ጉራ ፈርዳ ወረዳ ያፈናቀላቸው አማሮች ጉዳይ ያስከተለውን ከፍተኛ ተቃውሞ ተከትሎ ሁኔታውን የሚያድበሰብስና የተለመደውን የሃሰት ሪፖርት የሚያቀርብ ሆድ አደር ካድሬዎቹን ያካተተ ቡድን አጣሪ ኮሚቴ በሚል ተሰየመ

ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ የግንቦት 7 ምንጮች እንደገለጹት ቡድኑ የቤንች ማጂ ዞንና የጉራ ፈርዳ አስተዳዳሪዎችን እንዲሁም በህዝቡ ዘንድ የወያኔ የቀም በትር የሚባለውን የብአዴን አባላትን ያካተተ ነው። መኢአድ አንድ እንኳን ገለልተኛ አካል ያልተካተተበት በደል ፈጻሚዎቹ ብቻ የተሰባሰቡበት ይህ ኮሚቴ ትክክለኛ ሪፖርት ያቀርባል ብሎ እንደማያምን በመግለጽ ተቃውሞታል።

ወያኔ ይህንን ተራ የማጭበርበር ስልት በመጠቀም በምርጫ 97 የደረሰበት ሽንፈት ባሳደረበት ብስጭት ድምጻችን ይከበር ብለው በሰላማዊ መንገድ የጠየቁ ንጹሀን ዜጎች ላይ ጥይት በማርከፍከፍ ከ200 በላይ የሚሆኑትን በመግደል አጣሪ ኮሚቴ የሚል የሆድ አደሮች ስብስብ ሰይሞ የተወሰደው እርምጃ ተመጣጣኝ ነው የሚል ሪፖርት ማስቀረቡ የሚታወስ ነው።

አፍቃሪ ወያኔው ሪፖርተር በበኩሉ ራሳቸው በዳዮቹ ያቋቋሙት ይኼው ኮሚቴ ወደ ጉራፋርዳ ተጉዞ የገጠር ልማት ሠራተኞችን ማነጋገሩንና የአካባቢውን ነዋሪ ወክለው የሚናገሩ የገጠር ልማት ሠራተኞችም "ምንም በደል አልተፈጸመም" የሚል ምላሽ እንዲሰጡ መደረጉን ከመኢአድ መረጃ የደረሰው መሆኑን በመጥቀስ፣ በዚህ ሁኔታ ተቀነባብሮ የሚቀርብ የአጣሪ ኮሚቴ ሪፖርት ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይቻል እንደገለጹለት አስታውቋል።

መኢአድ እንደገለጸው የደቡብ ክልል መስተዳድር ማንም ሕጋዊ ሰው ከክልሉ አልተፈናቀለም በሚል ሰሞኑን መግለጫ ቢሰጥም መጋቢት 29 ቀን በጉራፋርዳ ሁለት ቀበሌዎችዉስጥ 22 ቤቶች መቃጠላቸውን፣ ስምንት ወፍጮዎችም ተነቃቅለው መወሰዳቸው ከአካባቢው መረጃ ደርሶታል፡፡

በሌላ በኩል የተፈናቃዮችን ጉዳይ የሚያጣራ ኮሚቴ ስለመቋቋሙ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ለሪፖርተር የገለጸው የሸፈራው ሽጉጤ አማካሪ አሚሳ ሚልኮ ክልሉን ለቀው እንዲወጡ የተደረጉት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ አካባቢው መጥተው ደን በመጨፍጨፍ በሕገወጥ መንገድ የሰፈሩ ሰዎች ናቸው ብሏል።

ይሄው እፍረተ ቢስ የወያኔ ተላላኪ አሚሳ ሚልኮ በጉራፋርዳ ወረዳ በሕጋዊ መንገድ መሬት ተረክቦ በአካባቢው ሲኖር የነበረ አንድም ሰው አልተፈናቀለም፡፡ አካባቢውን እንዲለቁ የተደረጉት ከየካቲት 2004 ዓ.ም በኋላ የመጡ ናቸው ሲል ሸምጥጧል፡፡ አሚሳ ሚልኮን የመሳሰሉ አባላትን ካካተተው አጣሪ ቡድን ምንም የማይጠበቅ ቢሆንም ዘረኛው መለስ ዜናዊና ቡድኑ ወያኔ የህዝቡን ግንዛቤ አስመልክቶ ያላቸው ንቀት እየጨመረ መጥቶ ጣራ መንካቱን የሚያመላክት ነው።

የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንት የሆነው ሽፈራ ሽጉጤ አፍቃሪ ወያኔ ለሆነ አንድ የፓልቶክ ስብስብ ባለፈው ቅዳሜ በሰጠው ቃለመጠይቅ ከክልሉ የተባረሩት መኢአድ ወደ ክልሉ በመላክ ያሰፈራቸው ናቸው በማለት የተለመደውን የበሬ ወለደ ፈጠራ ውንጀላ ማቅረቡን ለማወቅ ተችሎአል። ሚስኪን አርሶ አደሮችን በዘራቸው ምክንያት ከኖሩበትና ንብረት ካፈሩበት ይዞታቸው በግፍ ያባረረው ሽፈራ ሽጉጤ ሰዎችን በፖለቲካ እምነታቸው ምክንያት ማባረር ወንጀል እንዳልሆነ በማስመሰል ለመከላከል መሞከሩ መለስ ዜናዊ ምን አይነት ሂሊና ቢሶችን በቅጥረኝነት በዙሪያው እንዳሰባሰበ አመልካች ነው ተብላአል።

## በዘረኛው መለስ ዜናዊ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በሽብረተኝነት ተወንጅለው ከወያኔ ችሎት እየተመላለሱ ያሉት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና አንዱ አለም አራጌ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ለታሰሩበት ካሳ ተከፍሏቸውና ከሳሾቻቸው ተገቢውን የህግ ቅጣት አግኝቶ ወዲያውኑ ከእስር መፈታት የሚችሉ እንደሆነ አስመስክሮአል።

መላው ኢትዮጵያዊ እንደሚያውቀው በነዚህ የነጻነት ተፋላሚዎች ላይ የተመሰረተው ክስ የፖለቲካ ተቀናቃኞችን ለመምታት ሲባል የተቀነባበረ በመሆኑ ተከሳሾች ያቀረቡት ማስረጃ ምንም አይነት ፍትሃዊ ዳኝነት ሊያስጣቸው እንደማይችል ይታወቃል። ይህ በዚህ እንዳለ በነአንዱአለምና እስክንድር ነጋ ላይ የተመሰረተውን የፖለቲካ ክስ ሂደት በመከታተል የዘገቡ የፍትህና የነጋድራስ ጋዜጦች አዘጋጆች ችሎቱን የማንቋሸሽ እና አጠቃላይ ሂደቱን ተአማኒነት የሚያሳጣ ዘጋባ እያቀረቡ ነው በማለት የወያኔ አቃቤ ህግ ለፍርድ ቤቱ ላቀረበው ክስ አዘጋጆቹ በተናንትናው ችሎት ቀርበው መልሳቸውን ይሰጣሉ ተብሎ ቢጠበቅም ፤ የነጋድራስ አዘጋጅ በችሎቱ ሲገኝ የፍትህ ዋና አዘጋጅ የሆነው ተመስገን ደሳለኝ ግን ችሎት ላይ ሳይገኝ እንደቀረ ተዘግቦአል። የፍትህ ጋዜጣ አዘጋጅ የሆነው ተመስገን ደሳለኝ ችሎት ያልተገኘው መጥሪያ ስላልቀረበለት በመሆኑ ለፍርድ ቤቱ በመገለጡ መጥሪያ እንዲላክለትና በሚቀጥለው ቀጠሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠቱን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያመለክታል። በትናንትናው ችሎት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ልክ እንዳለፈው ጊዜ ተመስገን ያተመው የራሱን ቃል መሆኑን ለችሎቱ በድጋሚ ቢናገርም ከዳኞቹ ግሳጼ ተሰጥቶታል።

የፍትህና የነጋድራስ ጋዜጣ አዘጋጆች በአቃቢ ህግ ተብየው ክስ የቀረበባቸው የእስክንድር ነጋን ቃል አዛብተው አቅርበዋል በሚል ሰበብ መሆኑ መዘገቡ ይታወሳል።

## ምነው ዝም አላችሁ?:

ምን ነካው ጠበሉ ጸሎቱ ስግደቱ
የናት ያባት አምላክ የሰው ያራዊቱ
ምነው ዝም አላችሁ ሲረዝም ሌሊቱ
ጸሀይ ስትጠልቅብን ገና በጥዋቱ

የቁልቢ ገብሬል የወሊሶ ጠበል
የአርሲዋ እመቤት የወሎ አባ ጀበል
የባሌው ሼህ ሑሴን የአፋሩ ሱልጣን
መብተኛ እያለ ለጥጋብ ለቁንጣን
ምነው ዝም አላችሁ መጋኛ ሲመታን
ቤታችን ሳይጠፋ ጀበናና ዕጣን

እንሰብሰብ እንቢ እንናገር እንቢ
እየለቀቁብን ጥይት እንደ ርቢ
ታስረን ስንገረፍ በሰራነው ግቢ
እረ ዝም አትበሉ በአላህ በነቢይ

መስጊዱ ሲቃጠል ሲፈርስ ገዳሙ
እምነቱ ሲዋረድ ክርስቲያን እስላሙ
ምነው ዝም አላችሁ ቁሩና ይማሙ?

አሁን ነው መፋቀር አሁን ነው መጠንከር
በአይናውጣ ዘራፊዎች መጅሊሱ ሲደፈር
ባልጠፋ እርሻ ቦታ መነኩሴው ሲባረር

ምን ነካው ሃይቁ ወንዝና ጅረቱ
ምንም እንዳልሰማ ፈዝዞ መተኛቱ

አባይና አዋሽ ባሮና ሸበሌ
ፍንጫና ብላቴ ጊቤና ግንፍሌ
በለስና ጎጅብ ጨጨሆና ሚሌ
ምንው ጩከናችሁ አሞና ገናሌ
አፈር ይዞ ሩጫ እየተራብኩ እኔ

ተጠላልፈን ወድቀን እኛ ስንጫጫ
በተለይ ገናሌ አባይ አሞ ፍንጫ
ማነው ያስተማራችሁ አፈር ይዞ ሩጫ?

እኛ እየተፋጀን ስትሮጡ ዘርፋችሁ
ሶስት ሺ አመት ሙሉ ሳታዩን ቆማችሁ
ልመና ስንወጣ እናንተ እያላችሁ
መሬቱን መቦርቦር መሸርሸር አንሷችሁ
ትራንስፎርሜሽን ህዳሴ እያላችሁ
አዳ አስገባችሁን ቦንድ እያተማችሁ

ተራራች ኮረብቶች አዝጊአ አቤት በሉ
ራስ ዳሽን ባቱ ጉና ዳሞት ቱሉ
አይታችሁ እንዳላየ ኸረ ዝም አትበሉ

ሰምጥ ሸለቆአችን ሃይቁ ሲነሳ
ቆቃና አባያ አቢያታ አዋሳ
ጫሞና ላንጋኖ ዝዋይና ሸላ
ለአሞራው ሰልችቶት አምባዛና አሳ
ምነው ዝም አላችሁ ጩከናችሁሳ?

ፎቶ ጫሞ ሃይቅ ላይ ፊሌቶው ከአዋሳ
የአርባምንጭ የዝዋይ በየአይነቱ አሳ
ላንጋኖን ለአዳር ዝዋይን ለምሳ
እንዳማረን ቀረ ስንፋጭ በጎሳ

እኛም ተጠላልፍን እናንተም ፈራችሁ
የዳሎል ልጆች ከአመድ ተወልዳችሁ
ፍል ውሃው ሞቋችሁ ጨው እየበላችሁ
እሳተ ገሞራው ቀልጦ ሃሞታችሁ
ውሃዎች ሆናችሁ ውኃ እየጠማችሁ
ያህያ ልጅ በቀሎ እንደኛ ሆናችሁ
አሳውን ቱሪስቱን ማጥመዱን ትታችሁ
ኦሮሞ አፋር ኢሳ ደቡብ አያላችሁ
በክልል ሸኝሸና በዘር ተጣላችሁ

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

መካከኛ ሞገድ፡- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ፡- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org